በግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር
በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት
የሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ
ሚዛን

ጉዳዩ፡- የኮሌጁን የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት የመጨረሻ
የሥራ አመራር ሪፖርትን ይመለከታል፤

በርዕሱ የተጠቀሰውን የሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ የ2009 በጀት ዓመት ሂሣብ የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦችን የያዘ 41 ገጽ የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት (Final Management Letter) እና 29 ገጽ አባሪ በድምሩ 70 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን ልከናል፡፡ በመሆኑም በገጽ 71 በተመለከተው የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች አተገባበር መርዓ-ግብር ቅጽ መሰረት የተወሰዱ እርምጃዎች በአስቸኳይ እንዲላክልን እናሳስባለን፡፡

ከሰላምታ ጋር !

ሰለሞን መብራቱ
የልማትና ማኅበራዊ መሥሪያ ቤቶች
ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

ግልባጭ

- ☞ ለግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር ከ70 ገጽ አባሪ ጋር
- ☞ ለግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና
  ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ከ70 ገጽ አባሪ ጋር

አዲስ አበባ

የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# በግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር

# በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት

# የሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ

## የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት

## የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት

**ግንቦት 2010 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

# በግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር
# በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት
# የሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ
# የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት

## መግቢያ

ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ በአዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመሥሪያ ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት በቀድሞው እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር የ2009 በጀት ዓመት የሂሣብ መግለጫ ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ ሂሳቡን ኦዲት አድርገናል።

## ዓላማ

የዚህ ደብዳቤ ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶችን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ፣ የፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤቱና የኮሌጁ የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁቱና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱበት ለማድረግ ነው።

## የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት

ኦዲቱ የተከናወነው የዓለም አቀፍ የመንግሥት ኦዲት ደረጃዎችን (INTOSAI/ISA) መሰረት በማድረግ እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው። እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ (የኦዲት አስተያየት) ለመስጠት ያስችለናል።

## ኦዲታችን የሚያካትተው፡-

- ✓ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና መመርመርን፣
- ✓ የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣
- ✓ የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ለፌዴራል መንግሥት አጠቃላይ ዓመታዊ ገቢና ወጪ ሂሣብ መግለጫ ዝግጅት አግባብነት ያላቸው መሆኑን፣ ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል።

ከዚህም በተጨማሪ የሂሳብ መግለጫዎቹ ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና መመርመርን ይጨምራል።

የሂሳብ መግለጫዎቹ ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆናቸው በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል። አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል።

በመሆኑም በዚህ ሪፖርት ላይ ከተመለከቱት የአሰራርም ሆነ የሂሳብ አያያዝ ድክመቶች በተጨማሪ ሌሎች ድክመቶች ወይም ስህተቶች ሊኖሩ የሚችሉ ከመሆኑም በላይ የሂሳብ መግለጫውን ለማዘጋጀት የተዘረጉትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም።

የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ከዚህ ጋር የተያያዙ ግድፈቶችና ስህተቶች ሁሉ ሊታወቁ የሚችሉት ይህን አስመልክቶ ሰፊ ጊዜ በመውሰድ ልዩ የዝርዝር ኦዲት በጥልቀት ሲከናወን መሆኑን እንገልጻለን።

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ኃላፊነት ነው።

**<u>የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሐሳቦች</u>**

**የሚዛን ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅን በ**2009 **በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሐሳቦች ረቂቅ ሪፖርት ላይ ምላሽ እንዲሰጥ የካቲት** 13 **ቀን** 2010 **ዓ.ም በቁጥር** OFAGF-02.13/2/3 **በተጻፈለት ደብዳቤ መሰረት ኮሌጁ የካቲት** 22 **ቀን** 2010 **ዓ.ም በቁጥር መም**.08.04/863/2010 **በጻፈው ደብዳቤ ምላሽ ሰጥቷል። በመሆኑም ለሥራ አመራሩ የተዘጋጀው የመጨረሻው ሪፖርት እንደሚከተለው ቀርቧል።**

**1. <u>የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ</u>**

**1.1. <u>መደበኛ የሂሳብ ሚዛኑን ያልጠበቀ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ</u>፤**

**1.1.1. <u>ግኝት</u>**

**በበጀት ዓመቱ የሂሳብ መዝጊያ ሰኔ** 30 **ቀን** 2009 **ዓ.ም በጥሬ ገንዘብ ተቀጽላ ለጀሮች ላይ የተመለከተው ከወጪ ቀሪ ሚዛን** (Ending Balance) **በሂሳብ አያያዝ ሥርዓቱ መሰረት የዴቢት መደበኛ ሚዛናቸውን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ዴቢት ወይም ዜሮ ሚዛን መታየት ያለበት ቢሆንም ብር 293,367.62 ክሬዲት ሚዛን የሚያሳይ እና ሂሳቡም ካለፈው በጀት ዓመት ጀምሮ እየተንከባለለ የመጣ መሆኑ ታውቋል።** (**ለዝርዝረ አባሪ** 1 **ተያይዟል**)

**1.1.2. <u>ሥጋት</u>**

**ሂሳቦች መደበኛ የዴቢት ወይም የክሬዲት ሚዛናቸውን ያልጠበቁ ከሆነ በሂሳብ መግለጫዎቹ ላይ በየሒሳብ መደቡ የተመለከቱትን ሂሳቦች ትክለክለኛውን ሂሳብ እንዳያመለክቱ ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ።**

**1.1.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>**

**መደበኛ ሚዘናቸውን ያልጠበቁት የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ሁኔታ ተጣርቶ ተገቢው ማስተካከያ ሊሰራለት ይገባል። ለወደፊቱም ሂሳቦች መደበኛ የዴቢት ወይም የክሬዲት ሚዛናቸውን የጠበቁ ለመሆኑ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል።**

#### 1.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

በክፍሉ ውስጥ ያሉት ባለሙያዎች በስልጠና ባለመደገፋቸው በልምድ የሚሰሩና በኮሌጁ የውስጥ ቁጥጥር ባለመኖሩ የተፈጠረ ችግር ነው።

#### 1.1.5. የኦዲተሩ አስተያየት

የጥሬ ገንዘብ ሂሳቡ መደበኛ የዴቢት ሚዛኑን ያልጠበቀበት ምክንያት ተጣርቶና በተጨባጭ ማስረጃ ተደግፎ ተገቢው ማስተካከያ እንዲሰራለት፤ ለወደፊቱም በአመዘጋገብ ወቅት ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን።

## 2. የገቢ ሂሳብ

### 2.1. የሂሳብ መደቡን ጠብቆ ያልተመዘገበ የገቢ ሂሳብ፤

#### 2.1.1. ግኝት

የገቢ የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ል/ት/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ኮሌጁ በበጀት ዓመቱ ከግብርና ምርት ሽያጭ የሰበሰበውን ገቢ በሂሳብ መደብ 1455 እንዲሁም ከማታ ትምህርት የሰበሰበውን ገቢ ብር 882,656.62 በ1443 መመዝገብ በሂሳብ መደብ 1489 መመዝገቡ ታውቋል። ስለሁኔታው በ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ወቅትም አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም በአሁኑ ኦዲትም ሳይስተካከል በድጋሚ ተገኝቷል።

#### 2.1.2. ሥጋት

- በሂሳብ መግለጫው ላይ በየሂሳብ መደቦቹ ሥር ሊታይ የሚገባውን የሒሳብ ሚዛን ሊያዛባው ይችላል።
- ለሂሳብ ሪፖርቱ ተጠቃሚዎች ትክክለኛውን መረጃ እንዳይሰጥ ሊያደርግ ይችላል።

#### 2.1.3. የማሻሻያ ሃሳብ

በትክክለኛዉ የሂሳብ መደብ ላልተመዘገበው ሒሳብ ተገቢው ማስተካከያ እንዲሰራለት፤ ለወደፊቱም ኮሌጁ የሂሳብ ምዝገባ ሲያከናውን የገ/ኢ/ል/ት/ሚ/ር

ነሐሴ 1999 ዓ.ም ያወጣውን የሂሳብ አያያዝ ሥርዓትን ተከትሎ ምዝገባውን ማከናወን ይኖርበታል።

**2.1.4. <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>**

በተሰጠው የኦዲት ማሻሻያ ሀሣብ መሠረት ተስተካክሎ እየተመዘገበ ይገኛል።

## 3. <u>ተሰብሳቢ ሂሳብ</u>

### 3.1. <u>መደበኛ የሂሳብ ሚዛኑን ያልጠበቀ ተሰብሳቢ ሂሳብ</u>፤

**3.1.1. <u>ግኝት</u>**

በበጀት ዓመቱ የሂሳብ መዝጊያ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም በተሰብሳቢ ተቀጽላ ለጀሮች ላይ የተመለከተው ከወጪ ቀሪ ሚዛን (Ending Balance) በሂሳብ አያያዝ ሥርዓቱ መሰረት የዴቢት መደበኛ ሚዛናቸውን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የተሰብሳቢ ሂሳብ ዴቢት ወይም ዜሮ ሚዛን መታየት ያለበት ቢሆንም በ4203 የሂሳብ መደብ ብር 2,322.00 እንዲሁም በ4211 የሂሳብ መደብ ብር 2,355,699.89 በድምሩ ብር 2,358,021.89 ክሬዲት ሚዛን የሚያሳዩ እና አብዛኛው ሂሳቡም ካለፈው በጀት ዓመት ጀምሮ እየተንከባለለ የመጣ መሆኑ ታውቋል። (ለዝርሩ አባሪ 1 ተያይዟል)

**3.1.2. <u>ሥጋት</u>**

ሂሳቦች መደበኛ የዴቢት ወይም የክሬዲት ሚዛናቸውን ያልጠበቁ ከሆነ በሂሳብ መግለጫዎቹ ላይ በየሒሳብ መደቡ የተመለከቱትን ሂሳቦች ትክለክለኛውን ሂሳብ እንዳያመለክቱ ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ።

**3.1.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>**

መደበኛ ሚዘናቸውን ያልጠበቁት የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሁኔታ ተጣርቶ ተገቢው ማስተካከያ ሊሰራለት ይገባል። ለወደፊቱም ሂሳቦች መደበኛ የዴቢት ወይም የክሬዲት ሚዛናቸውን የጠበቁ ለመሆኑ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል።

#### 3.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

በክፍሉ ውስጥ ያሉት ባለሙያዎች በስልጠና ባለመደገፋቸው በልምድ የሚሰሩና በኮሌጁ የውስጥ ቁጥጥር ባለመኖሩ የተፈጠረ ችግር ነው።

#### 3.1.5. የኦዲተሩ አስተያየት

ተሰብሳቢ ሂሳቦቹ መደበኛ የዴቢት ሚዛናቸውን ያልጠበቁበት ምክንያት ተጣርቶና በተጨባጭ ማስረጃ ተደግፎ ተገቢው ማስተካከያ እንዲሰራለት፤ ለወደፊቱም በአመዘጋገብ ወቅት ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን።

### 3.2. በደንቡና በመመሪያው መሰረት ያልተወራረደ (ያልተሰበሰበ) ሂሳብ፤

#### 3.2.1. ግኝት

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ፤ በመመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ደግሞ ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል። ይሁንና ኮሌጁ በደንቡና በመመሪያው መሰረት የፈጸመ መሆኑ ሲጣራ በተለያዩ የተሰብሳቢ የሂሳብ መደቦች (ኮዶች)፡-

- ☞ ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ድረስ የቆየ ብር 685,171.88፣
- ☞ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ድረስ የቆየ ብር 458,370.46፣

በድምሩ ብር 1,143,542.34 በደንቡ መሰረት ሳይወራረዱ (ሳይሰበሰብ) በሂሳብ መግለጫው ላይ የሚታይ መሆኑ ታውቋል። በተወሰኑት ሂሳቦች ላይ በ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ወቅትም ሂሳቡ እንዲወራረድ አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም ሂሳቡ ሳይወራረድ ይገኛል። (ዝርዝሩ አባሪ 2 ተያይዟል)

#### 3.2.2. ሥጋት

በተሰብሳቢ ሂሳቦች ላይ ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል ካልተደረገ፡-

- ☞ የመንግሥት ገንዘብ ለታቀደለት ዓላማ መዋሉን ለማረጋገጥ ካለማስቻሉም በላይ ገንዘቡ ሳይሰበሰብ ሊባክን ይችላል።
- ☞ ገንዘቡ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ለማረጋገጥ አይቻልም።

### 3.2.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የቅድሚያ ክፍያ ሒሳቦች በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት እንዲወራረዱ (እንዲሰበሰቡ) ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል። ሊወራረዱ (ሊሰበሰቡ) የማይችሉ ከሆነ ደግሞ ሁኔታው ተጣርቶ ደንብና መመሪያውን ተከትለው እንዲሰረዙ መደረግ እንዳለበት በድጋሚ ለማሳሰብ እንወዳለን።

### 3.2.4. <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

ተሰብሳቢ ሂሳቡ ከሂሳብ አሰራር አንጻር መስተካከል አለበት። ነገር ግን ከወናው መሥሪያ ቤት መላክ ያለበት በጀት ባለመላኩ የሚያጋጥም ነው። በቀጣይ ግን ኮሌጁ ትኩረት በመስጠት ማጣራት ይኖርበታል።

### 3.2.5. <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

አብዛኛዎቹ ተሰብሳቢዎቹ ለረዥም ዓመታት እየተንከባለሉ የመጡ ሲሆን፣ ባለፉት በጀት ዓመታት ኦዲት ወቅትም መወራረድ (መሰብሰብ) የሚችሉት እንዲወራረዱ (እንዲሰበሰቡ)፤ መወራረድ (መሰብሰብ) የማይችሉ ከሆነ ደግሞ በደንቡና በመመሪያው መሰረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠባቸው ቢሆንም ተገቢው እርምጃ ባለመወሰዱ ተሰብሳቢ ሒሳቦቹ ከዓመት ወደ ዓመት እየተንከባለሉ ይገኛሉ። በተወሰነ መልኩ ሂሳቡን ለማወራረድ የተጀመረው ጥረት የሚደገፍ ቢሆንም በቀሪዎቹ ተሰብሳቢ ሂሳቦቹም ላይ በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳብ መሰረት ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ በድጋሚ እናሳስባለን።

## 4. ተከፋይ ሂሳብ

### 4.1. በወቅቱ ያልተከፈለ ወይም የተከፋይ ሂሳቡ ሁኔታ ተጣርቶ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ያልተደረገ ሂሳብ፤

#### 4.1.1. ግኝት

በኮሌጁ የሚገኙት ተከፋይ ሂሳቦችን ተገቢነት ለማረጋገጥ እንዲሁም መሥሪያ ቤቱ ያለበትን ተከፋይ ሂሳብ በወቅቱ ለሚመለከተው አካል የሚከፍል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከካፒታልና ከውስጥ ገቢ በጀት በተለያዩ የተከፋይ ሂሳብ ኮዶች (መደቦች)፡-

- ☞ ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ድረስ የቆየ ብር 148,496.82፣
- ☞ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ድረስ የቆየ ብር 381,077.27፣

በድምሩ ብር 529,574.09 ሳይከፈል በሂሳብ መግለጫው ላይ የሚታይ ሲሆን፣ በተወሰኑት ሂሳብ መደብ ላይ በ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ወቅትም የሂሳቡ ሁኔታ ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም እርምጃ እንዲወሰድ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል።

(ለዝርዝሩ አባሪ 3 ተያይዟል)

#### 4.1.2. ሥጋት

የተከፋይ ሂሳቡ ሁኔታ ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ ካልተወሰደ የሂሳብ ሪፖርቱን ተዓማኒነት ሊያሳጣው ይችላል።

#### 4.1.3. የማሻሻያ ሃሳብ

በፋይናንስ አስተዳደር ደንብና መመሪያ መሠረት ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ መከፈል ይኖርባቸዋል። ለረጅም ዓመታት ሲንከባለል የመጣውና ለማን እንደሚከፈል የማይታወቀው ተከፋይ ሂሳብ ሁኔታም ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል።

#### 4.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

የተከፋይ ሂሳቡ የሚታየው ከፌዴራል የሚላከው የጥሬ ገንዘብ በጀት ፍሰቱ በትክክል ባለመላኩ ከዓመት ወደ ዓመት የሚተላለፍ ችግር ነው። ነገር ግን አሰራሩ መስተካከል አለበት።

#### 4.1.5. የኦዲተሩ አስተያየት

ከላይ በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳብ መሰረት በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት ያልተከፈሉ ሂሳቦች እንዲከፈሉ፤ ሊከፈሉ የማይችሉ ከሆነ ግን በመመሪያው መሰረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ መደረግ ይኖርበታል።

## 5. የወጪ ሒሳብ

### 5.1. በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ላይ ተመዝግበው የተገኙ የጥሬ ገንዘብ ክፍያዎች ስለመኖራቸው፤

#### 5.1.1. ግኝት

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት የቼክ ወይም የባንክ ዝውውር የገንዘብ ክፍያን ለመመዝገብ የምዝገባ መነሻ ሰነድ በመሆን የሚያገለግለው የባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ሲሆን፣ የጥሬ ገንዘብ ክፍያ በገንዘብ ያዥ ሲፈጸም ደግሞ የምዝገባ መነሻ ሰነድ የሚሆነው የወጪ ማስመስከሪያ ለመሆኑ ተመልክቷል። በሌላ በኩል ደግሞ ጥሬ ገንዘብ ነክ ያልሆኑ የሒሳብ እንቅስቃሴዎችን ለመመዝገብ በምዝገባ መነሻ ሰነድነት የሚያገለግለው የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ለመሆኑ በሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያው ላይ ተገልጿል። በመሆኑም ከሌጁ የሂሳብ ምዝገባውን የሚያከናውነው በሂሳብ አያያዝ ሥርዓቱ ላይ በተመለከተው መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ ብር 231,826.62 የጥሬ ገንዘብ ክፍያዎች የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ተዘጋጅቶላቸው ተመዝግበው ተገኝተዋል።

(ዝርዝሩ አባሪ 4 ተያይዟል)

### 5.1.2. *ሥጋት*

የወጪ ሂሳብ ሰነዶቹ በሂሳብ አያያዝ ሥርዓቱ ላይ በተቀመጠው መሰረት ጥቅም ላይ የማይውሉ ከሆነ የመረጃውን ተጠቃሚዎች ሊያሳስቱ ይችላሉ።

### 5.1.3. *የማሻሻያ ሃሳብ*

የጥሬ ገንዘብ፣ የቼክ ወይም የባንክ ዝውውር የገንዘብ ክፍያዎች ሲፈጸሙ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት በተገቢው የሂሳብ ሰነድ እንዲመዘገቡ መደረግ ይኖርባቸዋል።

### 5.1.4. *የሥራ አመራሩ ምላሽ*

በተሰጠው የማሻሻያ ሀሣብ መሠረት ሙሉ በሙሉ ተስተካክሎ እየተሠራ ይገኛል።

### 5.1.5. *የኦዲተሩ አስተያየት*

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የቼክ ወይም የባንክ ዝውውር የገንዘብ ክፍያን ለመመዝገብ የምዝገባ መነሻ ሠነድ በመሆን የሚያገለግለው የባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ነው። ስለሆነም የምዝገባ ሰነድ መዘጋጀት ያለበት የወጣውን መመሪያ ተከትሎ መሆን ይኖርበታል። ስለሆነም ለወደፊቱ የምዝገባ ሰነዶች በመመሪያው መሰረት እንዲዘጋጁ ተገቢው ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል።

## 5.2. *ወጪ ማስመስከሪያ ደረሰኞች ላይ በጀት ስለመፈቀዱ እና ሂሳቡን በሚያረጋግጠው ሰው ያልተፈረመ ስለመሆኑ*፤

### 5.2.1. *ግኝት*

የገ/ኢ/ል/ት/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ መንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት እንዲሁም በፌዴራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 3/2003 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 6 ማናቸውም የሳጥንና የባንክ ሂሳብ ወጪ ከመሆኑ በፊት፡-

- ☞ ክፍያዎች ከመፈጸማቸው በፊት በወጪ ማስመስከሪያ ደረሰኞች ለክፍያው በጀት መኖሩን ባረጋገጠው ሰራተኛ መፈረም እንዳለበት፣

☞ እንዲሁም በወጪ ማስመስከሪያ ደረሰኞች ላይ ክፍያውን ባረጋገጠው ሰራተኛ መፈረም እንዳለበት፣ ተመልክቷል።

ሆኖም በኮሌጁ የወጪ ማስመስከሪያዎች (Payment Voucher) ላይ በናሙና ከታዩት የወጪ ሂሳቦች ውስጥ ብር 1,693,822.08 ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት በጀት ስለመፈቀዱ እንዲሁም ስለሂሳቡ ትክክለኛነት በወጪ ማስመስከሪያዎች ላይ በፊርማ የማይረጋገጥ መሆኑ ታውቋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 5 ተያይዟል)

#### 5.2.2. ***ሥጋት***

☞ ለየሂሳብ መደቦቹ (ኮዶቹ) የተፈቀደ በጀት ሳይኖር ክፍያ ሊፈጸም ይችላል።

☞ ክፍያዎቹ ላይ ስህተት ቢኖር ሳይታረሙ የሚታለፉበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል።

#### 5.2.3. ***የማሻሻያ ሃሳብ***

ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ለወጪው በጀት የተያዘ ለመሆኑ በቅድሚያ በወጪ ማስመስከሪያ ደረሰኞች ላይ እንዲረጋገጥ መደረግ ይኖርበታል።

#### 5.2.4. ***የሥራ አመራሩ ምላሽ***

በ2010 በጀት ዓመት በተሰጠው የኦዲት ማሻሻያ ሀሳብ መሰረት ሙሉ በሙሉ ተስተካክሎ እየተሰራ የሚገኝ ሲሆን፣ የ2009 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶችን በአባሪው መሰረት ሰነድ ክፍል ያሉ ሰነዶች ተለይተው ኮሚቴው ወደ ሥራ ሲገባ የሚፈረም መሆኑን እናረጋግጣለን።

### 5.3. ***አለአግባብ የተከፈለ ደመወዝ፤***

#### 5.3.1. ***ግኝት***

ኮሌጁ ለሠራተኞች በየወሩ የሚፈጽመው የደመወዝ ክፍያ ሰራተኞች በሥራ ላይ ለነበሩበት ጊዜ ብቻ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ መምህር ቸርነት ወርቁ የተባሉ የኮሌጁ ሰራተኛ መሥሪያ ቤቱን የካቲት 30 ቀን 2009 ዓ.ም ባመለከቱት መሰረት ከመጋቢት 1 ቀን 2009 ዓ.ም በገዛ ፍቃዳቸው ከሥራ የለቀቁ መሆኑ ታውቋል። ሆኖም ያልሰሩበት የመጋቢት ወር ሙሉ ደመወዝ ብር 5,615.00 የተከፈላቸው መሆኑ ታውቋል።

### 5.3.2. ሥጋት

- ☞ የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ ወጪ እንዲሆን ምክንያት ሊሆን ይችላል።
- ☞ ለውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም ምክንያት ሊሆን ይችላል።

### 5.3.3. የማሻሻያ ሃሳብ

አለአግባብ የተከፈለው ደመወዝ በአስቸኳይ ተመላሽ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ እንዳይከሰት ተገቢው ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል።

### 5.3.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

- ☞ በየወሩ በአማካኝ ከ4 እስከ 5 ሠራተኞች ከሥራ ገበታቸው የሚለቁ በመሆኑ ዝርዝር ከየስራ ክፍሉ ሲመጣ ከፍተኛ ጥንቃቄ ተደርጎ እየተናበበ ደሞወዝ ይከፈላል። ሆኖም የዚህ መምህር ደመወዝ ግን በስራ ጫና ምክንያት በስህተት ከለቀቁ በኋላ የወር ደሞወዝ እንዲከፈላቸው የተደረገ በመሆኑ ግለሰቡ ተመላሽ እንዲያደርጉ በህግ የሚጠየቁበት አግባብ የሚፈጠር ይሆናል።
- ☞ በኮሌጁ የውስጥ ኦዲተር ካለመኖሩም ጋር ተያይዞ በወቅቱ እርምጃ ሊወሰድበት አልተቻለም።

### 5.3.5. የኦዲተሩ አስተያየት

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ባወጣው የፌዴራል መንግሥት የገንዘብ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት ተራ ቁጥር 12(1ሀ) መሰረት ለደመወዝ ዝግጅት ሊሟሉ ከሚገባቸው መረጃዎች ውስጥ አንዱ የመሥሪያ ቤቱ የሥራ ክፍሎች የክፍሉ ሰራተኞች በሥራ ላይ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው። የሥራ ክፍሎቹ ይህንን መረጃ ወር በገባ በ20ኛው ቀን የፋይናንስ ተግባርን ለሚያከናውነው የሥራ ክፍል በግልባጭም የአስተዳደር ተግባርን ለሚያከናውነው የሥራ ክፍል ማሳወቅ እንዳለባቸው ተመልክቷል። በኮሌጁ ይህ አሰራር በአግባቡ ባለመተግበሩ ምክንያት ያለአግባብ የደመወዝ ክፍያ ሊፈጸም ችሏል። ስለሆነም በቀጣይ የሥራ ክፍሎቹ በመመሪያው መሰረት ሰራተኞች በሥራ ላይ መሆናቸውን እንዲሳውቁ፤ አለአግባብ የተፈጸመው ክፍያም ተመላሽ እንዲሆን መደረግ ይኖርበታል።

## 5.4. ከመመሪያ ውጭ የተከፈለ ውሎ አበል፤

### 5.4.1. ግኝት

ኮሌጁ ለመስክ ስራ ለሚወጡ ሰራተኞች የሚፈጽመው የውሎ አበል የፌዴራል ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ኃይል ሚኒስቴር ሰኔ 29 ቀን 2004 ዓ.ም በቁጥር ሲሰሚ/30/ጠ13/40/883 ባወጣው የውሎ አበል አከፋፈል መመሪያ መሰረት ማንኛውም የመንግሥት ሰራተኛ ከመደበኛ የስራ ቦታው ውጭ ወደ ሆነ ሌላ የስራ ቦታ ለስራ ጉዳይ ሄዶ ዕለቱን መመለስ ካልቻለ በአዲሱ የውሎ አበል አከፋፈል መመሪያ መሰረት ቁርስ፣ ምሳና እራት በተጠቀመበት ቦታ (ከተማ) እንዲሁም የአልጋ ክፍያ በጉዞ ወቅት ባደሩበት አካባቢ በወጣው የውሎ አበል አከፋፈል መሰረት በዝርዝር ታስቦ እንዲከፈል መመሪያው ያዛል። ኮሌጁ በዚሁ መሰረት የፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፡-

1. የኮሌጁ ለሚገኙ ሰራተኞች በተሰማሩበት የስራ መስክ የተሻለ አፈጻጸም አቅም እንዲኖር በማቀድ ከየካቲት 30 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ በኮሌጁ ግቢ ውስጥ ለተከታታይ 15 ቀናት የክህሎት ስልጠና በሰጠበት ወቅት፡-
   - ☞ ስልጠና ለሰጡ 17 መምህራን ከአራት ቀን እስከ ሰባት ቀን በጠቅላላው ብር 14,193.00 የዉሎ አበል ክፍያ ከመመሪያ ውጭ የተፈጸመ መሆኑ፣
   - ☞ ለድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች የምሳ አበል ብር 6,727.50 የተከፈለ መሆኑ፣
   - ☞ ስለስልጠናው ዝርዝር ሁኔታ የሚገልጽ ፕሮፖዛል ለኦዲት እንዲቀርብ ቢጠየቅም ሊቀርብ ያልቻለ መሆኑ፣

2. የኮሌጁ ሰራተኞች የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን ለመጎብኘት ሲሄዱ ክፍያው በአሶሳ የአበል መጠን ብር 171 መሰረት ተሰልቶ መከፈል ሲገባው ብር 200 በመከፈሉ:-
   - ☞ ለ65 ሰራተኞች በጠቅላላው ብር 11,960.00 በብልጫ ተከፍሎ መገኘቱ፣
   - ☞ የመንግሥት ተሿሚ ሳይሆኑ ለኮሌጁ ምክትል ዲን ለስምንት ቀን ብር 1,416.00 መከፈል ሲገባው በቀን 500 ሂሳብ በጠቅላላው ብር 4,000.00 በመከፈሉ ምክንያት በብልጫ ብር 2,584.00 ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፣
   - ☞ ለሶስት የኦዲዮ ቪዥዋል ሰራተኞችና ለጋዜጠኞች የስምንት ቀን የውሎ አበል በቀን ብር 200 በጠቅላላው ብር 1,600.00 ተከፍሏቸው

እያለ በድጋሚ ለ7 ቀን በቀን ብር 200.00 በጠቅላላ ለአራት ሰው ብር 4,200.00 ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፣

በጠቅላላው ከውሎ አበል መመሪያ ውጪ ብር 39,664.50 የውሎ አበል ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ ታውቋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 6 , 7 እና 8 ተያይዟል)

### 5.4.2. *ሥጋት*

የውሎ አበል ክፍያ የወጣውን መመሪያ ተከትሎ ካልተፈጸመ፡-

- የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ ወጪ ሊሆን ይችላል።
- የክፍያውን ትክክለኛነትና አግባብነት ለማረጋገጥ አይቻልም።

### 5.4.3. የማሻሻያ ሃሳብ

ከደንብና መመሪያ ውጪ የተፈጸመው ክፍያ ተመላሽ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም የውሎ አበል ክፍያ የወጣውን መመሪያ ተከትሎ እንዲፈጸም እንዲሁም የውሎ አበል ክፍያዎች ከመፈጸማቸው በፊት መመሪያው በሚፈቅደው አግባብ ለመፈጸሙ ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል እንዲደረግ እናሳስባለን።

### 5.4.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

1. ኮሌጁ ለሚገኙ ሰራተኞች በተሰማሩበት የሥራ መስክ የተሻለ አፈጻጸም አቅም እንዲኖር በማቀድ ከየካቲት 30 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ በኮሌጁ ግቢ ውስጥ ለተከተታይ 15 ቀናት የክህሎት ስልጠና በሰጠበት ወቅት የውሎ አበል ክፍያ የተፈጸመው፡-
   - አብዛኛዎቹ ሠራተኞች ከ7 ኪ.ሜ እና ከዚያ በላይ እየተጓዙ እዚሁ ውለው ስልጠናውን ሲከታተሉ ስለነበሩ ይህንን ታሳቢ በማድረግ የተከፈለ አበል ነው።
   - የአሠልጣኝ መምህራን ውሎ አበል ክፍያ የተፈጸመው ስልጠናውን ለመስጠት ከሥራ ሰዓት ውጭም ለስልጠና የሚያስፈልገውን ሞጁሎችን ያዘጋጁ በመሆኑ እንዲሁም ሥልጠናውን ለመስጠት ያበረከቱትን አስተዋጽኦ ግምት ውስጥ በማስገባትና የሙያ አበል ለመክፈል ባለመቻሉ የተከፈለ ነው።

2. የኮሌጁ ሠራተኞች የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን ለመጎብኘት ሲሄዱ የተፈጸመውን የውሎ አበል ክፍያ በተመለከተ፤

- በተራ ቁጥር 64፣ 65 እና 66 ለኦዲዮ ቪዥዋል ባለሙያ እና ጋዜጠኞች የተከፈለው የ8 ቀን ውሎ አባልና የ7 ቀን አበል ተጨማሪ አበል የተከፈለው ሌሎቹ ሰራተኞች የኮሌጁ ሰራተኞች በመሆናቸው የ7 ቀን አበል በራሳቸው እንዲሸፍኑና ተቋሙ የስምንት ቀን ውሎ አበል እንዲደግፋቸው በተደረሰው ስምምነት መሰረት ሲሆን እነዚህ ጋዜጠኞችና የኦዲዮ ቪዥዋል ባለሙያ በትብብር ከሌላ ተቋም የተጋበዙ በመሆናቸው እንዲሁም በጉብኝቱ ወቅት የተቀረጹ መረጃዎች ኢዲት ለማድረግና ለዜና ስርጭት ዝግጁ ለማድረግ ታሳቢ በማድረግ የተከፈለ ሲሆን በቀን 200 የተከፈለው ውሎ አበል በተመኑ መሰረት ተስተካክሎ ልዩነቱ የሚከፈል መሆኑን እንገልጻለን።
- በተራ ቁጥር 49 የመንግሥት ተሿሚ ሳይሆኑ ለኮሌጁ ምክትል ዲን የተከፈለው የተሿሚ አበልን በተመለተ ግለሰቡ ከሚያዝያ 7 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ በወቅቱ የግብርና ልማት ዘርፍ ሚኒስቴር ዴኤታ በነበሩት የአስተዳደርና ልማት ም/ዲን ሆነው የተሾሙና አጠቃላይ በሁሉም ኮሌጆች ዲንና ም/ዲኖች የተሿሚ አበል አከፋፈል በግብርና ቴ/ሙ/ት/ስ/ማስተባበሪያ ጽ/ቤት በኩል የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ማብራሪያ ተጠይቆ ምላሽ በመስጠቱ ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ በዚሁ አግባብ ክፍያ እየተፈጸመ የሚገኝ ነው።

### 5.4.5. የኦዲተሩ አስተያየት

የቀድሞው የግብርና ሚኒስቴር ታኅሳስ 7 ቀን 2006 ዓ.ም በቁጥር 18አጠፈ112/266 ስለኮሌጁ ተሿሚዎቹ የቀን አበል አከፋፈል ማብራሪያ እንዲሰጠው በጠየቀው መሰረት የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ታኅሳስ 7 ቀን 2006 ዓ.ም በቁጥር ሲ.ሰ.ሚ.መ30/ጠ13/47/201 በተጻፈ ደብዳቤ በሰጠው ማብራሪያ ኮሌጆቹን የሚያስተዳድሩ ኃላፊዎች የመንግሥት ተሿሚ መሆናቸው እስከተረጋገጠ ድረስ መመሪያው በሚያዘው መሰረት በተሿሚዎቹ ደረጃ የተፈቀደውን አበል ተጠቃሚ መሆናቸውን ገልጿል። በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 74 ከፍተኛ የመንግሥት የሲቪል ሹመት ሊሰጥ የሚችለው በጠቅላይ

ሚኒስትሩ ብቻ ነው። ስለሆነም በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ሚኒስቴር ደኤታ ለኮሌጁ በሹመት የተመደቡት ኃላፊ የመንግሥት ተሿሚ ናቸው ተብሎ ሊወሰድ አይችልም። በመሆኑም በማሻሻያ ሃሳቡ በተመለከተው መሰረት አለአግባብ የተከፈለው ክፍያ ተመላሽ እንዲሆን፤ ለወደፊቱ የውሎ አበል ክፍያ መንግሥት ያወጣውን የክፍያ መመሪያ ተከትሎ ለመፈጸሙ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን ።

## 5.5. በመረጃ ያልተደገፉ የሂሳብ ማስተካከያዎች፤

### 5.5.1. ግኝት

የምዝገባ ለውጦች ሲደረጉ የፋይናንስ ሥርዓትና መመሪያን መሰረት በማድረግ ተገቢው የሂሳብ ማስተካከያዎች የተሰራላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በኮሌጁ ለብር 6,761,600.38 በዴቢትና በክሬዲት የተሰሩት የሂሳብ ማስተካከያዎች የሂሣብ ምዝገባ ማዘዣ (ጆርናል ቫውቸር) የተዘጋጀላቸው ቢሆንም፡-

- ✓ ስህተቱ በየትኛው የወጪ ደረሰኞች ላይ እንደተፈፀመ፣
- ✓ የሂሣብ ማስተካከያው እንዲሠራ ያስፈለገበት ምክንያት፣

ማስተካከያ በተሰራበት የሂሣብ ምዝገባ ማዘዣ ላይ አይገለጽም። ሁኔታው የተሰራው ማስተካከያ ትክክለኛ መሆን ወይም አለመሆኑን ለማረጋገጥ አያስችልም። ከዚህም በተጨማሪ ማስተካከያ በተሰራበት ጆርናል ቫውቸር ላይ በአብዛኛው ያዘጋጀው ሥምና ፊርማ፣ ያጸደቀው ሥምና ፊርማ ያልተገለጸና ያልተፈረመ መሆኑ ታውቋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 9 ተያይዟል)

### 5.5.2. ሥጋት

የሂሣብ ማስተካከያው እንዲሠራ ያስፈለገበት ምክንያት እንዲሁም ስህተቱ በየትኛው የገቢና የወጪ ደረሰኞች ላይ እንደተፈፀመ ሳይገለጽ (ሳይታወቅ) እንዲሁም የተዘጋጀው ጆርናል ቫውቸር በሚመለከተው ሰራተኛና ኃላፊ ሳይፈረምና ሳይጸድቅ የሚሰሩ የሂሳብ ማስተካከያዎች ለጥፋትና ለጉድለት መንገድ ሊከፍቱ እና የሒሳብ መግለጫዎቹን ተዓማኒነት ሊያሳጣቸው ይችላሉ።

#### 5.5.3. የማሻሻያ ሃሳብ

በፋይናንስ ሥርዓትና መመሪያው መሰረት ለተሰሩት የሂሳብ ማስተካከያዎች ተገቢው መረጃ ሊቀርብላቸው ይገባል።

#### 5.5.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

የተፈጠረው ክፍተት በክህሎት እጥረት ምክንያትና በወጪዎች ከበጀት በላይ ሲፈጸሙ ለዝውውሩ ማስተካከያ እስኪደረግ ድረስ በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ከሪፖርት እንዲወጡ ተደርጎ ከዝውውር በኋላ የሚመለሱ በመሆኑ የተፈጠረ ክፍተት ሲሆን ከግኝቱ በኋላ ትክክለኛ ማጣቀሻ እየተጻፈ እየተሠራ ይገኛል።

#### 5.5.5. የኦዲተሩ አስተያየት

ስህተቶች ሲፈጠሩ የሂሳብ ማተካከያዎች ሊሰሩ ይችላሉ። ችግሩ ያለው የሂሳብ ማስተካከያ መሰራቱ ላይ አይደለም። ችግሩ የሂሳብ ማስተካከያ ሲሰራ ደጋፊ ማስረጃ እንዲያያዝ ወይም ማስተካከያ የተሰራበት ምክንያት፣ ስህተቱ በየትኛው ቫውቸር ላይ እንደተፈጠረ በአግባቡ ሊገለጽ ይገባል። ስለሆነም የሚሰሩት ማስተካከያዎች በተጨባጭ ማስረጃ ላይ እንዲደገፉ መደረግ ይኖርበታል።

### 5.6. ከግዥ ሂሳብ ላይ ያልተቀነሰና ያልተመዘገበ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የቅድሚያ ግብር ሂሳብ፤

#### 5.6.1. ግኝት

የካቲት 8/2002 ዓ/ም በቁጥር ታክ/ቀ/5/102 በገገርዉ ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም የገ/ኢ/ል/ት/ሚ/ር ባወጣዉ መመሪያ መሰረት ታክሱን የመሰብሰብ ኃላፊነት የተሰጣቸዉ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ከመጋቢት 1 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ ከብር 5,000.00 በላይ ከሚፈጸሙት ግዢ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያዉን በመቀነስ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ገቢ ማድረግ እንዳለባቸዉ፤ በተጨማሪም ከዕቃና የአገልግሎት ግዥዎች ላይ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 እንዲሁም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 78/1994 መሰረት የቅድሚያ ግብር (2%) መቀነስ እንዳለበት ተመልክቷል። ይሁን እንጂ ኮሌጁ የተለያዩ የዕቃና የአገልግሎት ግዥ ከታክሱ ተመዝጋቢዎች ላይ ሲፈጸም፦

1. ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 946320 ለተማሪዎች ቀለብ (ነጭና ቀይ ሽንኩርትና ድንች) ከመልካሙ በለጠ አትክልትና ፍራፍሬ መሸጫ ግዥ ሲፈጸም የተቀነሰው የቅድሚያ ግብር ብር 362.07፣
2. ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 946303 የተማሪዎች ቀለብ (ጤፍ፣ ሩዝ፣ አተር፣ ምስር ክክና እርድ) ከይማም መሀመድ እህል አቅራቢ ግዥ ሲፈጽም የተቀነሰው ብር 6,640.86 የቅድሚያ ግብር፣

በጠቅላላው ለተቀነሰው ብር 7,002.93 የቅድሚያ ግብር ምዝገባ ያልተከናወነ መሆኑ ታዉቋል፡፡

### 5.6.2. ሥጋት

- ☞ የመንግሥት ገንዘብ ለግብር ሰብሳቢው ባለሥልጣን በወቅቱ ገቢ ላይሆን ይችላል፡፡
- ☞ መንግሥት ያወጣውን ሕግ ተከትሎ ያለመፈጸም ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

### 5.6.3. የማሻሻያ ሃሳብ

ኮሌጁ መንግሥት ያወጣውን መመሪያ መሰረት የአገልግሎትና የዕቃ ግዥ ሲፈጽም በአዋጁ፣ በደንቡና በመመሪያው መሠረት የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የቅድሚያ ግብሩን በመሰብሰብ ለሚመለከተው አካል ገቢ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም ምዝገባ ያልተከናወነለት የቅድሚያ ግብር ሂሳብ ምዝገባ እንዲከናወንለትና ገንዘቡም ለሚመለከተው አካል ገቢ መደረጉ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

### 5.6.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

በተራ ቁጥር 1 እና 2 ለተጠቀሱት ደረሰኝ የተቆረጠላቸውና ለሃገር ውስጥ ገቢው በየወሩ የሚዘረዘረው ከፓዶቹ እየተዘጋ በመሆኑ ተዘርዝሮ ለሀገር ውሰጥ ገቢ የተደረገ ቢሆንም የሂሣብ ምዝገባ ላይ በተከፋይ ያልተያዘ በመሆኑ በቀጣይ በተከፋይ ምዝገባ የሚደረግ ይሆናል፡፡

### 5.6.5. የኦዲተሩ አስተያየት

የተከፋይ ሂሳቡ ካልተመዘገበ የወጪ ሂሳቡን ስለሚቀንሰ ተከፋይ ሒሳቡ እንዲመዘገብ መደረግ እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን፡፡

## 5.7. በተገቢው ሂሳብ መደብ ያልተወራረደ ሂሳብ፤

### 5.7.1. ግኝት

ኮሌጁ የሂሳብ እንቅስቃሴዎችን በተሟላና በተገቢው ሁኔታ የሚመዘግብ መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ ለቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ የተሰጠው ሂሳብ ብር 29,000.00 በዴቢት 4211 እና በክሬዲት 4103 ተብሎ የተመዘገበ ሲሆን፣ ለቅድሚያ ክፍያ ከተሰጠው ሂሳብ ውስጥ ብር 24,700.00 ሲወራረድ በዴቢት 6258 እና  በክሬዲት በ4211 ተብሎ መወራረድ ሲገባው በክሬዲት 4103 የሂሳብ መደብ ተብሎ ተወራርዶና ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ (ዝርዝሩ አባሪ 10 ተያይዟል)

### 5.7.2. ሥጋት

በየሂሳብ ኮዶቹ የተመለከተው የሂሳብ ሚዛን ትክክለኛውን ሚዛን እንዳያሣዩ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

### 5.7.3. የማሻሻያ ሃሳብ

ለሂሳቡ ተገቢውን የማስተካከያ ምዝገባ ማከናወን ይኖርበታል ለወደፊቱም ምዝገባዎች ከመከናወናቸው በፊት የምዝገባው ትክክለኛነት መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

### 5.7.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

ለሂሳብ ማስተካከያ መደረግ አለበት የተሰጠውን የኦዲት ማስተካከያውን ተቀብሎ የሂሳብ ማስተካከያ የሚሰራለት ይሆናል፡፡

### 5.7.5. የኦዲተሩ አስተያየት

ኮሌጁ የወጪ ሂሳቦችን ሲያወራርደ በተገቢው የሂሳብ መደብ የማይመዘግብ ከሆነ የተዘጋጀውን የሂሳብ መግለጫ ተዓማኒነት ሊያሳጣው የሚችል እና

በሚሰጠው የኦዲት አስተያየት ላይ ተጽህኖ የሚሳድር  በመሆኑ ተገቢው ማስተካከያ ሊሠራለት ይገባል።

## 5.8. <u>በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገቡ የወጪ ሂሳቦች</u>፤

### 5.8.1. <u>ግኝት</u>

የወጪ ሂሳቦች የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ት/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከታች ለተመለከቱት ብር 182,915.31 ክፍያዎች በተገቢው የሂሳብ መደብ ሳይመዘገቡ ተገኝተዋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 11 ተያይዟል)

### 5.8.2. <u>ሥጋት</u>

- ☞ የተዘጋጀዉን የሂሳብ መግለጫ ታዓማኒነት ሊያሳጣዉ ይችላል።
- ☞ በ2009 በጀት ዓመት በሚታየው የሂሳብ መግለጫ ላይ በየሂሳብ መደቡ ሊታይ የሚገባውን የገንዘብ መጠን በትክክል እንዳይታይ ምክንያት ሊሆን ይችላል።

### 5.8.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

በትክክለኛዉ የሂሳብ መደብ ላልተመዘገበው ሒሳብ ተገቢው ማስተካከያ እንዲሰራለት፤ ለወደፊቱም ኮሌጁ የገ/ኢ/ል/ት/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ያወጣውን የሂሳብ አያያዝ ሥርዓትን ተከትሎ ምዝገባውን ማከናወን ይኖርበታል።

### 5.8.4. <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

- ♦ በመዘጋገብ ችግር፣ በስራ ጫናና በክህሎት ማነስ የተፈጠር ችግር በመሆኑ በቀጣይ ቻርት ኦፍ አካዉንቱን በማንበብና በማየት በትክክለኛው የሂሳብ መደብ የሚመዘገብ ይሆናል።
- ♦ በ6310 የሂሳብ መደብ በጀት ያልጸደቀ በመሆኑ በሚቀርበው የሂሳብ መደብ  ምዝገባ ተከናውኗል።
- ♦ በ6271 የተመደበው በጀት በማለቁ ምክንያት ለወጪዉ የሚቀርበው የሂሳብ መደብ የምርምር ወጪ በመሆኑ ሂሳቡ 6223 ሊመዘገብ ችሏል።

#### 5.8.5. የኦዲተሩ አስተያየት

የበጀት ህጉ በሚፈቅደው አግባብ በጀትን አዛዋውሮ መጠቀም እንጂ በጀት ስለሌለው ወይም ስላለቀ ተብሎ ባልተፈቀደ የሂሳብ ኮድ ምዝገባ ማከናወን ተቀባይነት የለውም። ከዚህም በተጨማሪም ኮሌጁ የሂሳብ ሰራተኞች ስልጠና የሚያገኙበትን መንገድ ከዋናው መሥሪያ ቤት ጋር በመነጋገር ማመቻቸት ይኖርበታል።

### 5.9. በፋይናንስ አሰራር ሥርዓት ላይ የታዩ ክፍተቶች፤

#### 5.9.1. ግኝት

የኮሌጁ የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት፣ የሰነድ አያያዝና አመዘጋገብ ሥርዓት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ነሀሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት የአሰራር ክፍተቶች ታይተዋል።

- ለሰራተኛ የሚሰጥ የቅድሚይ ክፍያ ሂሳብ ሳይወራረድ ሌላ የቅድሚያ ክፍያ የሚሰጥ መሆኑ፣
- ሰነዶች በኤይቤክስ "IBEX" ከተመዘገቡ በኋላ በምዝገባው ላይ ስህተት ሲገኝ የሂሳብ ማስተካከያ እንዲሰራላቸው ይደረጋል። ሆኖም የመጀመሪያውን የምዝገባ መነሻ ሰነድ ላይ የተመለከተው ግማሹ እንዲታጠፍ (VOID) ወይም ዝርዝ ድልዝ መሆኑ፣
- አልፎ አልፎ የቅድመ ክፍያዎች የተወራረዱባቸው የምዝገባ ማዘዣ ላይ የወጪ ማዘዣው ደረሰኝ ቁጥር የማይጠቀስ በመሆኑ ቅድሚያ ክፍያ የተፈጸመባቸውን ሰነዶች ለማግኘት አስቸጋሪ መሆኑ፣
- ወጪዎች የተወራረዱባቸው የምዝገባ ማዘዣዎች ከጥራዙ ላይ ተቀዶ ከደጋፊ ሰነዶች ጋር የማይያያዙ መሆኑ፣
- የተጨማሪ እሴት ታክስና የቅድሚያ ግብር መሰብሰቢያ ደረሰኞች ሂሳብ ክፍል መዘጋጀትና መጠበቅ ሲገባቸው በግዥ ሰራተኛ እጅ የሚዘጋጁና የሚጠበቁ መሆኑ፣ ታውቋል። ቀደም ሲል በተደረገው ኦዲት ወቅትም

በተወሰኑት ላይ እንዲስተካከሉ አስተያየት የተሰጠባቸው ቢሆንም ሳይስተካከሉ ባሉበት ሁኔታ ይገኛሉ።

### 5.9.2. ***ሥጋት***

- ☞ *መጀመሪያ የተሰጡት የቅድሚያ ክፍያዎች ሳይወራረዱ ሌላ የሚሰጥ ከሆነ ለተሰብሳቢ ሂሳብ ማበጥና በወቅቱ አለመወራረድ ምክንያት ሊሆን ይችላል።*
- ☞ *ለውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም ምክንያት ሊሆን ይችላል።*
- ☞ *ሰነዶችን በቀላሉ አግኝቶ የሂሳቦቹን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አዳጋች ሊሆን ይችላል።*
- ☞ *ለሰነዶች መጥፋት ምክንያት ሊሆን ይችላል።*

### 5.9.3. ***የማሻሻያ ሃሳብ***

- ☞ *ሌላ የቅድሚያ ክፍያ* (*አድቫንስ*) *ከመሰጠቱ በፊት አስቀድሞ የተሰጠው የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ መወራረዱ መረጋገጥ ይኖርበታል።*
- ☞ *ሁሉም የሂሳብ ሰነዶች በሂሳብ ክፍል ሊቀመጡ ይገባል።*
- ☞ *ሰነዶች በአይነታቸው ተለይተውና በቀላሉ ሊገኙ በሚችሉበት አግባብ ተደራጅተው መቀመጥ ይኖርባቸዋል።*

### 5.9.4. ***የሥራ አመራሩ ምላሽ***

- ☞ *የፊቱ ሣይወራረድ ተጨማሪ ክፍያ የሚፈፀም መሆኑ ከደንብና መመሪያ ውጭ ከመሆኑም ባለፈ የተሰብሳቢ ሂሳብን የሚያሳብጥ ነው። ነገር ግን ሹፌሮችና አንዳንድ ሠራተኞች መስክ ሲወጡ የመጀመሪያውን ያወራርዱ በሚባልበት ጊዜ ከኃላፊዎች የስራው አንገብጋቢነትን በመግለፅና ሲመለሱ ያወራርዳሉ እየተባለ በክፍሉ ጫና እየተደረገብን በመሆኑ ነው።*

- ☞ *ስህተት ሲኖር በጆርናል ቫወቸር ማስተካከያ መደረጉ የሂሳብ አሰራር ደንብ የሚደግፍ ቢሆንም የመጀመሪያውን ሰነድ መሰረዝ* (VOID) *ማድረግ ግን በክህሎት ክፍተት ምክንያት የተፈጠረ ችግር ነው። ምክንያቱም ምንም አይነት የሂሳብ አያያዝ ስልጠና ያልተሰጠ በመሆኑ እንደዚህ አይነት ችግሮችን ማስተካከል አልተቻለም።*

☞ አብዛኛዎቹ ላይ እየተጠቀሰ የሚሰራ ቢሆንም ጥቂት ሰነዶች ግን በሥራ ጫና ሳይጠቀስባቸው ታልፏል፡፡ ለቀጣይ በደንብ እየታየ የሚሰራ ይሆናል፡፡

☞ በሥራ ጫና ምክንያት ተረስተው ሳይበጠሱ ቀርተው እንጂ በተጨማሪም የቦክስ ፋይል እጥረት በመኖሩ ቦክስ ፋይል እስኪገዛ ድረስ እዛው ፓድ ላይ እና ደጋፊ ያላቸውም የJV ቁጥር ተፅፎ በክላሰር ተቀምጦ ፋይል እስኪገኝ በመቆየታቸው አታችመንት የሌላቸው ምዝገባወች ተረስተው የቀሩ በመሆናቸው አሁን ግን ሁሉም ተበጥሰው በፋይል እንዲታሰሩ ይደረጋል፡፡

☞ ይህ አሰራር ከቀድሞ ጀምሮ እየተሰራበት ያለ ቢሆንም ደረሰኞችን ለሂሳብ ክፍል እንዲሰጡ ግዥዎች ቢጠየቁም በስማችን የወጣውን ፓድ አንሰጥም ስላሉ መተግበር አልተቻለም፡፡

## 5.10. <u>ኮሌጁ የግዢ እቅድ ያላዘጋጀ ስለመሆኑ</u>፤

### 5.10.1. <u>ግኝት</u>

ሰኔ 2002 ዓ.ም የወጣዉ የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 3 አንቀጽ 8 ቁጥር 1 ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤትና በስሩ የተደራጁ አካላት የታቀዱ የስራ ፕሮግራሞቻቸዉን ተግባራዊ ለማስደረግ የሚያስፈልጋቸዉን ግዥ በወቅቱ ለመፈጸም የሚያስችል በመርሃ ግብር የተደገፈ የግዥ ዕቅድ ማዘጋጀት እንደሚገባና ዕቅዱም ለግዢ ኤጀንሲ መላክ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ሆኖም ኮሌጁ በ2009 በጀት ዓመት የግዥ እቅድ ያላዘጋጀ መሆኑ ታውቋል፡፡

### 5.10.2. <u>ሥጋት</u>

☞ ያለእቅድ የሚገዛ ግዥ የመንግሥት ገንዘብ ያላግባብ እንዲወጣ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

☞ በመመሪያው መሰረት የግዥ እቅድ ያለማዘጋጀት ተጠያቂነት ሊያሥከትል ይችላል፡፡

#### 5.10.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

በግዥ አፈጻጸም መመሪያው መሰረት ኮሌጁ የግዥ እቅድ በማዘጋጀት በኮሌጁ ኃላፊ ጸድቆ ለግዥ ኤጀንሲ እንዲላክ መደረግ ይኖርበታል።

#### 5.10.4. <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

ክፍሎች በወቅቱ የግዥ ፍላጎታቸውን የማያቀርቡ በመሆኑ በአብዛኛው ጊዜ ፍላጎት የሚቀርበው የበጀት አመቱ ከተጋመሰ በኋላ በመሆኑ ሲሆን፣ በአሁኑ ሰዓት ግን እየተስተካከለ ይገኛል።

#### 5.10.5. <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

ለወደፊቱ ኮሌጁ የግዥ እቅድ በማዘጋጀት በወቅቱ ለግዥ ኤጀንሲ መላክ ይኖርበታል።

## 6. <u>ንብረት</u>

### 6.1. <u>በንብረት አያያዝ ላይ የታዩ ክፍተቶች</u>፤

#### 6.1.1. <u>ግኝት</u>

የኮሌጁ የንብረት አስተዳደር በመንግሥት የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በተጨማሪም ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው የመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት የሚፈጸም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. በንብረት አስተዳደር መመሪያው መሠረት የስቶክ መዛግብቶችን የመያዝና ስቶክ የመረከብ እንዲሁም ወጪ የማድረግ ኃላፊነቶች ለአንድ ሠራተኛ መሰጠት እንደሌለባቸው የተመለከተ ቢሆንም በኮሌጁ በሁሉም የንብረት ዕቃ ግምጃ ቤቶች የንብረት ገቢና ወጪ ደረሰኝ (ሞ/19 እና ሞ/22) የማዘጋጀትና የስቶክ ምዝገባ የማከናወን የንብረት መጠበቅ ኃላፊነቶች ሥራ  በንብረት ግምጃ ቤቶቹ ሰራተኞች የሚከናወን መሆኑ፤
2. ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም በመምህራን ቤት ውስጥ የሚገኙ ንብረቶች በቆጠራ ያልተካተተ መሆኑ በተጨማሪም ቆጠራው

በመዝገብ ላይ (በእስቶክ ካርድ) ላይ ከተመለከተውና ከወጪ ቀሪ ጋር እንዲመዛዘን ያልተደረገ መሆኑ፤

3. የሚያገለግሉና የማያገለግሉ ዕቃዎችን ለመለየት በማያስችል ሁኔታ ተደባልቀው የተቀመጡ መሆኑ፤
4. በእርዳታ እና በስጦታ የሚገቡ እቃዎች ዋጋ ያልተተመንላቸው መሆኑ፤
5. የእስቶክ ምዝገባ ወቅታዊ ያልተደረገ መሆኑ፤
6. ለቋሚ እቃዎች መለያ ታግ ቁጥር ያልተለጠፈላቸው መሆኑ፤
7. የኮሌጁ የግቢው አጥር በአግባቡ ያልተከለለ እና አብዛኛው ክልሉ ክፍት መሆኑ፤
8. ብዛቱ 39 የሚሆን HP, ብዛቱ 72 Canaan፣ ብዛቱ 28 Brother TNO4M ብዛቱ 12 HP 610A እና ብዛቱ 21 Ink toners 92A በጠቅላላው 172 አገልግሎት መስጠት የማይችል በተለያየ ጊዜ ከእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ሚኒስቴር በስጦታ የመጣ የፕሪንተር ቀለም ካሉት ኮምፒውተሮች ጋር የማይገጥም በስቶር ውስጥ ተከማችቶ የሚገኝ መሆኑ እና ባገለገሉ አቃዎች ማስቀመጫ ግምጃ ቤት ደግሞ ከ200 በላይ የሚሆን የተለያየ ቁጥር ያላቸው አሮጌ ጎማ፣ አምስት ፕሮጀክተር፣ በርካታ ዴስክቶፕ ኮምፒዩተሮች በተለያየ ቦታ፣ ላፕቶፕ ኮምፒዩተሮች፣ ሁለት ፍሪጅ፣ ብዛት 25 የሚሆኑ ፋይል ካቢኔት ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣
9. ከአላጌ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ በስጦታ መልክ የመጡ ስድስት ሳጥን የታሸጉ የላብራቶሪ እቃዎች ከሶስት አመት በላይ ሳይከፈቱና አገልግሎት ላይ ሳይውሉ የሚገኙ መሆኑ፤

ታውቋል። በአብዛኛዎቹ ላይ ባለፉት በጀት ዓመታት ኦዲት ወቅትም ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠባቸው ቢሆንም እርምጃ ሳይወሰድ ባሉበት ሁኔታ የሚገኙ መሆኑ ታውቋል።

(በከፊል የፎቶ ማስረጃ በአባሪ 15 ተያይዟል)

### 6.1.2. ሥጋት

ኮሌጁ መንግሥት ባወጣዉ የንብረት አስተዳደር አዋጅና መመሪያ መሰረት የማይፈጸም ከሆነ፡-

- ✓ ለንብረት ቁጥጥር ሥርዓት መዳከም ምክንያት ሊሆን ይችላል።
- ✓ የመንግሥት ንብረት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል።

### 6.1.3. የማሻሻያ ሀሳብ

የንብረት አስተዳደሩ መንግሥት ባወጣው የንብረት አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ መሠረት እንዲስተካከልና እንዲፈጸም ትኩረት ተሰጥቶት ተገቢው ሥራ መሰራት ይኖርበታል።

### 6.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

1. ኮሌጁ ካለበት የሰው ሃይል እጥረት ምክንያት የተፈጠረ በመሆኑና ቢፒአር (BPR) በሚያዘው መሰረት ተገቢው ምደባ ያልተደረገለት በመሆኑና ጥያቄው ከክፍሉ በየጊዜው እየተጠየቀ በመሆኑ የሰው ኃይል ሲሟላ የሚስተካከል ይሆናል።

2. በቆጠራ ወቅት መምህራን ለክረምት ትምህርት ባለመኖራቸው የነበረ ሲሆን ከመጡ በኋላ ማስታወቂያ በመለጠፍ እንዲያስቆጥሩ ጥረት እየተደረገ ይገኛል።

3. የንብረት መጋዝን ጥበት እንዳለ ይታወቃል። ችግሩን ለመቅረፍ ግንባታ እንዲካሄድ ጥያቄ በመጠየቅ ላይ እንገኛለን።

4. ከእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ተልከው በመጋዝኑ የቆዩትን እንዲሁም ከቻይና መንግሥት በእርዳታ ያገኛቸውን ንብረቶች የሰጠን ሲሆን ሲመጡ ዋጋቸው ያልተሞላ በመሆኑ እኛም ለአሰራር የተቸገርን በመሆኑ ነው።

5. ለክፍሉ የተመደቡ አዳዲስ ባለሙያዎች ላይ የክህሎት ክፍተት ያለ ሲሆን አሁን በመስተካከል ላይ ይገኛል።

6. በሂደት ላይ ያለ ይገኛል።

7. በጀት ተጠይቆ በሂደት ላይ ይገኛል። በተጨማሪም በአጎራባች ካሉ ግለሰቦች ጋር የድንበር ችግር ያለ በመሆኑ ነው።

8. ከእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር የተገኙና በመቀያየር ለመጠቀም በባለሙያ ምክር የመጣ ሲሆን ለመጠቀም በሂደት ላይ ያለ ይገኛል።

9. እቃው ለትምህርት ክፍሎች የመጣ ሲሆን በተደጋጋሚ እንዲያወጡና እንዲጠቀሙ ቢጠየቅም ምላሽ ሊሰጠን አልቻለም።

#### 6.1.5. <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

የንብረት አስተዳደሩን ውጤታማ፣ ቀልጣፋና የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱን የተጠናከረ ለማድረግ ይቻል ዘንድ መንግሥት ያወጣውን የንብረት አስተዳደር ሥርዓት ተከትሎ ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል።

### 6.2. <u>በተሽከርካሪ ስምሪት፣ አያያዝና አጠቃቀም ላይ የታዩ ክፍተቶች</u>፤

#### 6.2.1. <u>ግኝት</u>

የኮሌጁ የተሽከርካሪ ሥምሪት፣ አያያዝና አጠቃቀም በፌዴራል መንግሥት የተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. መሥሪያ ቤቶች የተሽከርካሪዎችን የነዳጅ ፍጆታ ለመከታተልና መዝግቦ ለመያዝ እንደደረጃቸው የተሽከርካሪዎች የኪሎ ሜትር ቆጣሪ ጌጅ የተሟላና በትክክል የሚሰራ መሆኑን በየጊዜው በመከታተል ማረጋገጥ እንዳለባቸው የሚደነግግ ቢሆንም በኮሌጁ ይህ የማይደረግ መሆኑ፤ (ለምሳሌ ያህል የጭነት አይሱዙ ታርጋ ቁጥር 4-03042 እና ቤላሩስ ትራክተር)

2. ለበላይ ኃላፊዎች እና ለኃላፊዎች ከሚመደቡ ተሽከርካሪዎች በስተቀር እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የፈጀው የነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪሎ ሜትር መጠን ጋር እየተመዘገበ ተገቢዉ ሪፖርት በየወሩ የማይቀርብ መሆኑ፣

3. **አራት ሞተር ሳይክሎች (የሰሌዳ ቁጥር ኮድ** 4-0786 **ኢ.ት፣ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ** 4-0354 **ኢ.ት፣ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ** 4-0353 **እና የሰሌዳ ቁጥር ኮድ** 4-1812) ***በብልሽት ምክንያት ያለአገልግሎት ቆመው የሚገኙ መሆኑ፣***
4. **ኮሌጁ የሚጠቀምበት ቤላሩስ ትራክተር ሰሌዳ ቁጥርና ሊብሬ የሌለው *መሆኑ፣***

***ታውቋል።***

### 6.2.2. ***<u>ሥጋት</u>***

- ***በወጣው የተሽከርካሪዎች መመሪያ መሰረት ያለመፈጸም በውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ ላይ ክፍተት ሊፈጥር ይችላል።***
- ***መወገድ ያለባቸው ንብረቶች በወቅቱ ካልተወገዱ ለከፋ ብልሽት ሊዳረጉና ዋጋቸው ሊቀንስ እንዲሁም በቀላሉ ለጥፋትና ለብክነት ሊዳረጉ ይችላሉ።***

### 6.2.3. ***<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>***

- ✓ ***መንግሥት ለኃላፊዎች ከሚፈቅደው በስተቀር ሁሉም ተሽከርካሪዎች የኮሌጁን አርማ በሁለቱም የፊት በሮች ላይ መለጠፍ ይኖርባቸዋል።***
- ✓ ***በመመሪያው መሰረት የእያንዳንዱ ተሽከርካሪ የኪሎ ሜትር ቆጣሪ ጌጅ የተሟላና በትክክል የሚሰራ መሆኑን በየጊዜው በመከታተል መረጋገጥ ይኖርበታል።***
- ✓ ***በመመሪያው መሰረት የእያንዳንዱ ተሽከርካሪ የፈጀው የነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪሎ ሜትር መጠን ጋር እየተመዘገበ ተገቢዉ ሪፖርት በየወሩ መቅረብ ይኖርበታል።***
- ✓ ***መወገድ ያለባቸው ተሽከርካሪዎች በመመሪያው መሰረት እንዲወገዱ፣ ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የሚችሉት ደግሞ እንዲጠገኑ መደረግ ይኖርበታል።***

### 6.2.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

1. የሚስቲቡሽ መኪና የኪሎ ሜትር ቆጣሪው የሚሰራ ሲሆን የነዳጅና የናፍጣ ልኬቱ ጊዜ ያለፈበት ሲሆን አሁን የምናስለካ መሆኑን እናሳውቃለን። ቤላረስ ትራክተሩን ወደፊት የምንሰራበት ይሆናል። በተጨማሪም የነዳጅ ክትትል ቁጥጥር ሥራ የተሽከርካሪዎች ስምሪትና ጥገና ኃላፊ ስራውን ከለቀቀበት ከሀምሌ 2008 ጀምሮ የተሽከርካሪዎች ስምሪት የሚሰጠው ነዳጅ የሚፈቀደውና የሚጸድቀው በአ/ተ/ጉ/ም/ዲን እና በንብረት አስተዳደር ሲሆን ምዝገባውም የሚካሄደው በንብረት አስተዳደር በመሆኑ ክፍተቱ ሊፈጠር ችሏል። ሆኖም ለወደፊቱ በጥልቀት የምንሰራበት ይሆናል።

2. በየወሩ ሪፖርት በተመለከተ በኮሌጁ የተቀጠረው የስምሪትን ጥገና ክፍል ኃላፊ ከሐምሌ ወር 2008 ዓ.ም ጀምሮ ከሥራ ከለቀቀ በኋላ በቦታው ሌላ ሰራተኛ እንዲመደብ ተጠይቋል። ነገር ግን ሰራተኛ ስላልተመደበ ሪፖርቱ በየወሩ ሊቀርብ አልቻለም።

3. ከተጠቀሱት ሞተር ሳይክሎች የሰሌዳ ቁጥር 4-0786 እና 4-0353 ሲሆን ለነዚህም ጥገና ለማስደረግ በፕሮፎማና በጨረታ ለማሰራት በአካባቢው የተሟላ የሞተር ሳይክል ጠጋኝ ባለመኖሩ ሲሆን፣ ሌላ አማራጭ እንዲፈለግ ለግዥና ሽያጭ ከንብረት አስተዳደር ማስታወሻ ቀርቧል።

4. ቤላሩስ ትራክተሩ ንብረትነቱ በኮሌጁ የሚታወቀው የግብርና ሚኒስቴር (የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር) ቢሆንም የባሌበትነት ደብተሩ ከእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር እንዲጠየቅ ለአስ/ተ/ጉ/ም/ዲን ጥያቄ ቀርቧል። በተጨማሪም ክትትል እየተደረገበት ይገኛል።

### 6.2.5. የኦዲተሩ አስተያየት

ኮሌጁ በፌዴራል መንግሥት የተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 እንዲሁም በንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት ማስተካከል ይኖርበታል።

## 7. በጀት

### 7.1. ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለ በጀት ከ10% በላይ ያልተሰራበትና ከበጀት በላይ የወጣ ሂሳብ፤

#### 7.1.1. ግኝት

ለኮሌጁ ለ2009 በጀት ዓመት ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው የካፒታልና ከውስጥ ገቢ የወጪ በጀት በሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር ከ10% በላይ፡-

- ✓ ከካፒታል በጀት ብር 2,430,466.01፤
- ✓ ከውስጥ ገቢ በጀት ብር 314,915.60፤

በድምሩ ብር 2,745,381.61 ሥራ ላይ ያልዋለ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከካፒታል በጀት ብር **981,397.70** ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ መደረጉ ታውቋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 12 ተያይዟል)

#### 7.1.2. ሥጋት

- ☞ የወጪ ሂሣብ በጀቱ በእቅዱ መሠረት አለመፈፀሙ የኤጀንሲውን ዓመታዊ የሥራ ውጤት ዝቅ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ የበጀት ዕቅዱን ትክክለኛነት ላያመለክት ይችላል።
- ☞ በበጀት ሕጉ መሰረት የበጀት ዝውውር ሳይጠየቅ ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተፈቀደው በጀት በላይ መጠቀም ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል።

#### 7.1.3. የማሻሻያ ሃሳብ

ኮሌጁ የበጀት ዕጥረት ካጋጠመው በቅድሚያ የበጀት ሕጉን ተከትሎ የበጀት ዝውውር መጠየቅ ይኖርበታል። ከዚህም በተጨማሪ ሐገሪቷ ያላትን ውስን በጀት በማብቃቃት በተገቢው ሥራ ላይ ማዋል ይቻል ዘንድ በተለይም በጎላ ሁኔታ ጥቅም ላይ ሳይውሉ በቀሩት የሂሳብ ኮዶች ላይ በበጀት እቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ወቅት ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል።

#### 7.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

- ♦ በመደበኛ የጥሬ ገንዘብ ሳይለቀቅ በመቅረቱና ከውስጥ ገቢም የታቀደውን ያህል ገቢ መሰብሰብ ባለመቻሉ በጥሬ ገንዘብ እጥረት ምክንያት ሳይሰራበት የቀረ ነው።
- ♦ ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ የተፈጸመው ወጪ ለሠራተኛ ደመወዝ፣ ለኃላፊዎችና ሾፌሮች ጥቅማጥቅም የሚከፈል ወጪዎች ሲሆን በእነዚህ ኮዶች ኮሌጁ ያቀደውና ክፍያ ያጸደቀው በጀት በማነሱ እንዲሁም መንግስት በሀገር ደረጃ ለመምህራንና ሠራተኞች ደመወዝ ማሻሻያ ሲያደርግ ይህንን የሚመጥን በጀት ጥያቄ ለሚመለከተው አካል ቢቀርብም ጭማሪው መምጣት ባለመቻሉ የተፈጠረ ችግር ነው።

#### 7.1.5. የኦዲተሩ አስተያየት

- ✓ ኮሌጁ በበጀት ዕቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ላይ ተገቢ የሆነ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል። በተጨማሪም መሥሪያ ቤቱ የበጀት አጠቃቀሙ ላይ ክትትል በማድረግ እና የማይጠቀምበትን በጀት ለይቶ በማውጣት የበጀት እጥረት ላለባቸው መሥሪያ ቤቶች የበጀት ዝውውር ተደርጎ ጥቅም ላይ እንዲውል በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር በኩል የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር እንዲያውቀው መደረግ እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን።
- ✓ ኮሌጁ በያዘው ዕቅድ መሰረት ገቢውን መሰብሰብ ካልቻለ በተጨባጭ ማስረጃ ላይ ተደግፎ የገቢ እቅዱን መከለስ ይኖርበታል።

## 8. ልዩ ልዩ

### 8.1. በ2007 በጀት ዓመት በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ ያልተወሰደባቸው ግኝቶችን በተመለከተ፤

#### 8.1.1. ግኝት

የፌዴራል ዋና ኦዲተር የ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ መግለጫዎችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርጎ ሙያዊ አስተያየትና የማሻሻያ ሃሳቦች

ያቀረበ ሲሆን፣ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ የተወሰደባቸው መሆኑ ሲጣራ፡-

1. ኮሌጁ ከሰበሰበው የተጨማሪና እሴት ታክስ ብር 538,154.23 ውስጥ ብር 308,154.23 እንዲሁም ግዥ ሲፈጽም ተቀናሽ የተደረገው የቅድሚያ ግብር ብር 118,497.26 ውስጥ ብር 86,309.74 ለሚመለከተው የገቢ ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት ገቢ ከመደረጉ በፊት ወዲያዉኑ ተቀናሽ እንደተደረገ ምዝገባ እንዲከናወን ያልተደረገና ክፍያው ለመፈጸሙም ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤

2. በፋይናንስ መመሪያው መሰረት ማስረጃ ካልቀረበለት የወጪ ሂሳቦች ብር 1,623,558.73 ውስጥ ለብር 886,996.88 ማስረጃ የቀረበለት ሲሆን፣ ለቀሪው ለብር 736,561.85 በዚህ በጀት አመትም የወጪ ሂሳብ ማስረጃዎች ሊቀርብላቸው ያልቻለ መሆኑ፤ (ለዝርዝሩ አባሪ 13 ተያይዟል)

3. ኮሌጁ የመምሕራን መኖሪያ ቤት ግንባታ እስክንድር ታዬ የህንጻ ሥራ ተቋራጭ እንዲያከናውን በፈጸመው ውል የተፈጸሙ ክፍያዎችና የአመዘጋገብ ሥርዓቱ መመሪያውን ተከትሎ የተፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

   - ብር 49,047.43 በወጪ ያልተመዘገበ ሂሳብ መኖሩ፣
   - ብር 312,068.34 በክፍያ ሰርተፊኬቱ ላይ ተቀንሶ ቢታይም ክፍያው ሲፈጸም ያልተቀነሰና ያልተመዘገበ የተጨማሪ እሴት ታክስ መኖሩ፣
   - ብር 49,047.43 ተቀንሶ ያልተመዘገበ የመያዣ ሂሳብ መኖሩ፣
   - ብር 18,724.11 ከክፍያው ላይ እንዲቀነስ ቢታዘዝም ክፍያው ሲፈጸም ያልተቀነሰና ያልተመዘገበ የቅድሚያ ግብር ሂሳብ መኖሩ፣
   - ብር 330,792.34 በብልጫ የተከፈለ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ መኖሩ፣

   (ለዝርዝር አባሪ 14 ተያይዟል)

ተገልጾ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም በዚህ በጀት ዓመት ኦዲት ወቅትም ተገቢው እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ ታውቋል።

### 8.1.2. ሥጋት

ኮሌጁ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ የማይወሰድ ከሆነ፦

- ☞ በኦዲት ሪፖርት በሚሰጠው አስተያየት መሰረት በወቅቱ ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ያለመውሰድ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል።
- ☞ ለውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም፣ ለመንግሥት ገንዘብ መባከን እና አለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ይችላል።

### 8.1.3. የማሻሻያ ሃሳብ

በኦዲት ግኝቶች ላይ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ፤ ለወደፊቱም በኦዲት ሪፖርት በሚሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር እንዲደረግ በድጋሚ እናሳስባለን።

### 8.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

- ✓ በወቅቱ የነበረው የሂሳብ አሰራር ክፍተት እንዳለበት የኦዲት መግለጫ መታየቱ እና የተሰጠው አስተያየትን ለመተግበር አሁን ላይ ያለውን ሂሳብ ጋር እንዴት እንደሚስተካከል የክህሎት ክፍተት በስልጠና ቢደገፍ ገ/ኢ/ል/ት/ሚ በመጠየቅ ለማስተካከል እንሰራለን።
- ✓ የቅድሚያ ግብር ሳይቀነስ ገንዘብ ለግዥ ሠራተኛ በሆኑት በአቶ ንጋቱ ብርሀኑ ስም ወጪ ቢሆንም ገቢ አደርጋለሁ ከማለት ውጭ ያስገቡትን ደረሰኝ እንዲያመጡ ቢጠየቁም ሊያቀርቡ አልቻሉም። ለኮሌጁም ኃላፊዎች ቢገለፅም ክትትል አልተደረገም።
- ✓ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የተገኘው ገንዘብ ፈሰስ መደረግ ሲገባው ፈሰስ ያልተደረገው በወቅቱ መለቀቅ የሚገባው ገንዘብ ከፌደራል ባለመለቀቁ ምክንያት በኮሌጁ ወጪ ሆኖ ይገኛል።
- ✓ ኦዲተሮች ለሂሳብ ምርመራ በመጡበት ወቅት ምክንያቱ ባልታወቀ ምክንያት ወደ ሌላ የሥራ ክፍል እንድዛወር በመደረጉ የተጠየቀው ሠነድ ሙሉ በሙሉ ቀርቧል ማለት ባይቻልም ቀድሞ አልቀረበም የተባለው ሠነድ ውስጥ የተገለጸው እንዳለ ሆኖ የአመዘጋገብ ችግር

ቢኖርም ሠነዶች ግን እዚያው በሂሳብ ክፍልና በሠነድ ክፍል እንዳሉ መግለፅ ይቻላል።

#### 8.1.5. የኦዲተሩ አስተያየት

ለኮሌጁ ተመሳሳይ ለሆኑ ግኝቶች በተደጋጋሚ የኦዲት አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም በአስተያየቱ መሰረት መረጃዎችን አሰባስቦና ማጣራትን አድርጎ እርምጃ ከመውሰድ ይልቅ በየበጀት ዓመቱ ኦዲት ወቅት የተለያዩ ተቀባይነት የሌላቸውን ምክንያቶችን መደርደሩ ተቀባይነት አይኖረውም። ይልቁንም በኮሌጁ ውስጥ ያለውን የዶክመንቶች አያያዝ ድክመት በግልጽ የሚያመለክት መሆኑን መገንዘብና መረዳት ያስፈልጋል። ስለሆነም ለሚሰጡት የኦዲት አስተያየቶች ትኩረት ሰጥቶ በአፋጣኝ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል።

### 8.2. የትምህርት ዕድል ተጠቃሚ ሆነው ግዴታቸውን ያልተወጡ መምህራንን በተመለከተ፤

#### 8.2.1. ግኝት

ኮሌጁ ለሚሰጠው የትምህርት ዕድል የግዴታ ውል የሚያስገባ፣ ዋስ የሚያስጠራ መሆኑን እና የትምህርት ዕድል ያገኙት መምህራን ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ግዴታቸውን የሚወጡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በኮሌጁ በመምህርነት ተቀጥረው ሲያገለግሉ የነበሩ 8 (ስምንት) መምህራን በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የሁለተኛ ዲግሪያቸውን እንዲማሩ የተፈቀደላቸውና ከኮሌጁም ጋር ውል የፈጸሙ ሲሆን፣ በገቡት ውል መሰረት ህጉን ካፈረሱ የወጪው 15 በመቶ ታክሎበት ለመክፈል ወይም ተመጣጣኝ አገልግሎት ለመስጠት ውል የገቡ እና ዋስትና ያስያዙ ቢሆንም መምህራኖቹ የገቡትን ግዴታ ሳይወጡ፡-

1. መምህር በለጠ ጥላሁን ከጥቅምት 1/2008 ዓ.ም ጀምሮ፣
2. መምህር ወገኔ ተፈራ ከህዳር 1/2004 ዓ.ም ጀምሮ፣
3. መምህር አሸብር በርሄ ከህዳር 3/2005 ዓ.ም ጀምሮ፣
4. መምህር ረጋሳ ቤኛ ከህዳር 1/2003 ዓ.ም ጀምሮ፣
5. መምህር መርከቡ ጌታቸው ከጥቅምት 1/2003 ዓ.ም ጀምሮ፣
6. መምህር አዲሱ በዛብህ ከህዳር 1/2003 ዓ.ም ጀምሮ፣

7. መምህር ሚሊዮን ጤናው ከጥቅምት 30/1998 ዓ.ም ጀምሮ፣

8. መምህር ሙሉብርሀን ባይሳ ከህዳር 1/2003 ዓ.ም ጀምሮ፣

ሥራቸውን ለቀዋል። ሆኖም ግለሰቦቹ በገቡት ግዴታ መሰረት እርምጃ እንዲወሰድ ቀደም ሲል በተደረገው ኦዲት ወቅትም አስፈላጊው አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ ታውቋል።

### 8.2.2. ሥጋት

- ☞ የመንግሥት ገንዘብ ያለአግባብ ወጪ መሆኑን ሊያመለክት ይችላል።
- ☞ ኮሌጁ መምህራንን በማሰልጠን ሊያገኝ የሚገባውን ጥቅም ያሳጣል።

### 8.2.3. የማሻሻያ ሃሳብ

ኮሌጁ በውሉ መሰረት መምህራኖቹ አገልግሎቱን እንዲሰጡ ወይንም ገንዘቡን እንዲከፍሉ ማድረግ ይኖርበታል። መምህራኖቹ ገንዘቡን ለመክፈል ፍቃደኛ ሆነው ካልተገኙም በሕግ አግባብ እንዲጠየቁ መደረግ እንዳለበት በድጋሚ ለማሳሰብ እንወዳለን።

### 8.2.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

- ♦ በተራ ቁጥር 4, 5, 6 የተጠቀሱትን ኮሌጁ በሚዛን መደበኛ ፍርድ ቤት ክስ መስርቶ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ካዩ በኋላ የግዴታ ውል የተገባው በፌዴራል ግብርና ሚኒስቴር በመሆኑ ኮሌጁ ክስ ለመመስረት ስልጣን የለውም በሚል ብይን የሰጠ በመሆኑ ኮሌጁ የሶስቱንም መምህራን መረጃ ለግብርና ቴ/ሙ/ት/ሥልጠና ማስተባበሪያ የላከና ማስተባበሪያውም ለፌዴራል ግብርና ሚኒስቴር ህግ ጉዳዩች ዳይሬክቶሬት ክስ እንዲመሰረት በማስታወሻ ገልጿል።
- ♦ በተራ ቁጥር 7 ላይ የተጠቀሱት መምህር ሚሊዩን ጤናው በተመሳሳይ መልኩ ውል የተገባው በፌዴራል ግብርና ሚኒስቴር በኩል መሆኑን እንገልጻለን።

## 8.3. ያለአግባብ ጥቅም ላይ እየዋለ ያለ መኖሪያ ቤት፤

### 8.3.1. ግኝት

በኮሌጁ ግቢ ውስጥ ያሉት ቤቶች ለታለመላቸው ዓላማ ስለመዋላቸው ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ አንድ የዞኑ አስተዳራሪ እና የጀርመን ዜግነት ያላቸው የቤንች ቋንቋ ላይ ጥናት የምያደርጉ ሴት በግቢ ውስጥ ቤት ተሰጥቷቸው ለረጅም አመታት እየኖሩበት የሚገኙ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። (ለዝርዝሩ የፎቶ አባሪ 14 ተያይዟል)

### 8.3.2. ሥጋት

ቤቱ ማግኘት የሚገባቸው መምህራን ቤት በማጣታቸው ኮሌጁ ለመምህራኑ ለቤት ኪራይ የሚፈጽመው ክፍያ ሊጨምር ይችላል።

### 8.3.3. የማሻሻያ ሃሳብ

በኮሌጁ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የቤት እጥረት በመኖሩ ምክንያት ኮሌጁ ለመምህራኖች ለቤት ኪራይ አበል ወጪ እያደረገ ይገኛል። ስለሆነም ቤቶቹ በአስቸኳይ ተለቀው ለመምህራኖቹ መሰጠት ይኖርባቸዋል።

### 8.3.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

ቀደም ሲል በትውስት ተሰጥተው የነበሩ ቤቶች ከዚያ በላይ ስለነበሩ በተደረገው ጥረት አብዛኛዎቹ ቤቶች ተመልሰው በቤት ኪራይ አበል ይኖሩ ለነበሩ መምህራን በሙሉ ቤት ተሰጥቷቸው የአበል ወጪው በሙሉ እንዲቆም ተደርጓል። ቀሪዎቹንም ቤቶች በተጀመረው መሰረት በውይይትና መተማመን በመፍጠር እንዲመለስ በማስተባበሪያው ኃላፊ በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ክትትል ተደርጎ እንዲመለሱ ይደረጋል።

## 8.4. የውስጥ ኦዲት ክፍሉ የሰው ኃይል የሌለው ስለመሆኑ፤

### 8.4.1. ግኝት

በፋይናንስ አዋጅ ቁጥር 648/2001 እና በፋይናንስ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 970/2008 እና አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው መመሪያ ቁጥር 47/2009 መሰረት እንዲሁም በሚኒስትሮች ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 61 ንዑስ

አንቀጽ 3 መሰረት እያንዳንዱ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የዉስጥ ኦዲት ክፍል በየሩብ አመቱ የመሥሪያ ቤቱ ሥራ አመራርና ሠራተኞች ኃላፊነታቸዉን በብቃት መወጣት እንዲችሉ በተዘረጋዉ የዉስጥ ቁጥጥር ሥርዓት በሥራ ላይ ባሉት ህጎችና የአሰራር ሥርዓቶች መሰረት ስራዎች መከናወናቸዉን ኦዲት እያደረገ በመመሪያዉ ላይ በተቀመጡት ግዜ ዉስጥ ለመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊና ለእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ሪፖርት የሚያደርግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ለውስጥ ኦዲት ክፍሉ በመዋቅር የተፈቀደው የሰው ኃይል 3 ሲሆን አሁን በስራ ላይ የሚገኝ ሰራተኛ የሌለ በመሆኑ ምክንያት በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር መመሪያ መሰረት የየሩብ ዓመቱን ሂሳብ ኦዲት ያላደረገና የፈሰስ ሪፖርት ያልቀረበ መሆኑ ታውቋል፡፡

### 8.4.2. ሥጋት

የውስጥ ኦዲት ክፍሉ በሰው ኃይል እንዲሞላና ክፍተቶች እንዲስተካከሉ ካልተደረገ፡-

- ☞ የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬቱ የሚያከናውነው የኦዲት ሥራ የሚፈለገውን ደረጃና ጥራት እንዳይጠብቅ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡
- ☞ በቀላሉ ሊቀረፉ የሚችሉ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ድክመቶች ሳይታዩ ሊታለፉ ይችላሉ፡፡
- ☞ የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬቱን የኦዲት ሥራ የተሟላ አያደርገውም፡፡

### 8.4.3. የማሻሻያ ሃሳብ

የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬቱ፡-

- ☞ በአዲሱ የፋይናንስ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 970/2008 እንዲሁም አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው መመሪያ ቁጥር 47/2009 መሰረት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የውስጥ ኦዲት ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ተጠሪነት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር እንዲሆን የተደረገ በመሆኑ፣ ለውስጥ ኦዲት ክፍሉ በመዋቅሩ በተፈቀደው መሰረት ተገቢው የሰው ኃይል እንዲሟላለት የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር የውስጥ ኦዲት

ዳይሬክቶሬትን በመጠየቅ የተሟላና ብቁ የሆነ የሰው ኃይል በመመደብ (በመቅጠር) የሥጋት አካባቢዎችን ለይቶ በመመሪያው ላይ በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የኦዲቱን ሥራ እንዲያከናውን፤

☞ በመመሪያው መሰረት ዓመታዊ እቅድ በማዘጋጀትና የፈሰስ ሪፖርት እና የየሩብ አመቱን ሂሳብ ኦዲት በማድረግ የኦዲት ሪፖርቱን ለእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት እንዲያቀርብ፤

መደረግ ይኖርበታል።

8.4.4. <u>*የሥራ አመራሩ ምላሽ*</u>

ከሁለት ዓመታት በላይ ለሚሟላት በሚዲያ ማስታወቂያ ወጥቶ ባለሙያ ባለመገኘቱ ነው። ቢዘገይም አሁንም በዚህ በጀት አመት ሰራተኛ ለማግኘት ጥረቱ የቀጠለ ስለሆነ እንደተገኘ ቅጥሩን በመፈጸም በአስተያየቱ መሰረት እንዲስተካከል ይደረጋል። አስተያየቱንም ተቀብለናል።

## 8.5. <u>*የሥጋት ተጋላጭነት ግምገማ ያልተደረገ ስለመሆኑ*</u>፤

### 8.5.1. <u>*ግኝት*</u>

በፌዴራል መንግሥት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003 መሰረት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የተቋቋሙበትን ዓላማዎች ለማስፈጸም ዕቅዶችና ዝርዝር የዕለት ተዕለት ተግባራት በማከናወን ሂደት የሚከሰቱ ችግሮችንና የተጋላጭነት ደረጃ ለመለየት የውስጥና የውጪ ኦዲተሮችንና ሌሎች የሚመለከታቸውን ባለሙያዎች በመጠቀም የሥጋት ምንጮች ዳሰሳ ማካሄድ እንዳለባቸው ተመልክቷል። ሆኖም ኮሌጁ የሥጋት ምንጮች ዳሰሳ፣ የተጋላጭነት ደረጃ መለየት እና የሥጋት ተጋላጭነት ፍተሻ ያላደረገ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል።

### 8.5.2. <u>*ሥጋት*</u>

የሥጋት ተጋላጭነት ዳሰሳ ጥናት ተደርጎ የመፍትሄ አቅጣጫ ካልተቀመጠ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች ኮሌጁ ዓላማውን እንዳያሳካ እንቀፋት ሊሆኑ ይችላሉ።

### 8.5.3. የማሻሻያ ሃሳብ

ኮሌጁ የሥጋት ተጋላጭነት ዳሰሳ በየጊዜው ቢደርግ በውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ድክመት የተነሳ ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ለይቶ ቅድመ ጥንቃቄ ለመውሰድ የሚኖረውን ጥቅም ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በመመሪያው መሰረት የሥጋት ተጋላጭነት ዳሰሳ ማድረግ ይጠበቅበታል። ስለሆነም በመመሪያው መሰረት የስጋት ተጋላጭነት ዳሰሳ እንዲደረግ እናሳስባለን።

### 8.5.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

እስከአሁን ኦዲተር ለመቅጠር ተደጋጋሚ ሙከራ ተደርጎ ባለመገኘቱ በገጠመን ችግር የዘገየ ቢሆንም በቅርቡ እየተስተናገደ ባለው ቅጥር ኦዲተር ሊገኝ እንደሚችል ከውድድር ምዝገባው ማረጋገጥ ስለተቻለ ይህ ከተሳካ ቅጥሩ እንደተፈፀመ ስራውን ወዲያውኑ የምናስጀምር መሆኑን እንገልፃለን።

### 8.5.5. የኦዲተሩ አስተያየት

የሥጋት ተጋላጭነት ግምገማ የሚደረገው ኮሌጁ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማስፈፀም በሚያደርገው እንቅስቃሴ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ሥጋቶችን በመለየትና ምንጫቸውን በማወቅ፣ የሥጋት ደረጃና (Level of Risk) የተጋላጭነት አቅም (Probability of Occurrence) ተገንዝቦ ይህንን ሥጋት ለመቀነስ ከተቻለም ለመከላከል የሚያስችል ሥርዓት ለመዘርጋት ነው። ስለሆነም ኮሌጁ ሊሟሉ የሚገባቸውን ሁኔታዎች በማሟላት በመመሪያው መሠረት ተቋማዊ የሥጋት ተጋላጭነት ግምገማ ቢያደርግ ጠቃሚነቱ የጎላ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን።

## 8.6. ክፍት የስራ መደቦችንና የሰዓት መቆጣጠሪያን በተመለከተ፤

### 8.6.1. ግኝት

ኮሌጁ ባለው የሰው ሀብት አስተዳደር የእድገት የቅጥርና የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ተገቢነትን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. ኮሌጁ በዕቅድ የያዛቸውን ተግባራት በአግባቡ ለመፈጸም ይችል ዘንድ ክፍት የሥራ መደቦችን በሰው ኃይል መሙላት እንዳለበት ይታመናል። ሆኖም መሥሪያ ቤቱ በመዋቅር ከተፈቀደለት 498 የስራ መደቦች ውስጥ

በሰው ኃይል የተሞላው 310 ሲሆን 188 (38%) የሥራ መደቦች ክፍት መሆናቸው፤

2. የአገልግሎት ሰጪና የአስተዳደር ሰራተኞች የስራ ሰዓት መቆጣጠሪያን በሰራተኞቹ ከተፈረመ በኋላ የቀሩትን ሰራተኞች በየጊዜው ክትትል ተደርጎ ቀሪ (አብሰንት) የማይደረግ መሆኑ፤
3. መመህራንን በተመለከተ አቴንዳንስ ወይም የሰአት መቆጣጠሪያ የማይሞላ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

### 8.6.2. ሥጋት

- ☞ የተሟላ የሰው ኃይል ባለመኖሩ ምክንያት ኮሌጁ ዕቅዱን እንዳያሳካ ምክንያት ሊሆን እንዲሁም በአሰራር ላይ ክፍተት ሊፈጥር ይችላል፡፡
- ☞ በስራ ላይ ለማይገኝ ሰራተኛ ደመወዝ ሊከፈል ከመቻሉም በተጨማሪ ለውስጥ ቁጥጥር መዳከም ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

### 8.6.3. የማሻሻያ ሃሳብ

ኮሌጁ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት ያስችለው ዘንድ ክፍት የስራ መደቦችን በቅጥርና በእድገት እንዲሞሉ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ሰራተኞችን በተመለከተ የስራ ሰዓት መቆጣጠሪያ በአግባቡ በመጠቀም በሰው ኃብት የስራ ክፍል እንዲቀመጥ መደረግ ይኖርበታል፡፡

### 8.6.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

- ♦ ወሳኝ በሆኑ የስራ መደቦችን ብቻ በሰው ኃይል ለማሟላት ታስቦ በኮሌጁ ሥራ አመራር አስተያየት መሰረት በሂደት እንዲሟላ የሚደረግ ይሆናል፡፡
- ♦ ክፍት የስራ መደቡ በሰራተኛ እንዲሟላ በመጠየቂያ ቅፅ (ተቀፅላ 1) መሰረት ክፍት የስራ መደቦች የሚሞሉት በሥራ ሂደቱ ጥያቄና ፍላጎት በመሆኑና ጥያቄ ባለመቅረቡ ቅጥር አልተካሄደም፡፡ በተለይም ከ2007 በጀት ዓመት ጀምሮ ከበጀት ጋር ተያይዞ በጀት የለም በመባል ከፕሮጀክት ማስ/ጽ/ቤት ጋር ግልጸኝነት ባልተፈጠረ ሁኔታ ከበላይ አመራር ደብዳቤዎች በቅጥርና በደረጃ ዕድገት ጥንቃቄ እንዲደረግ

በመጻጻፍ በአጠቃላይ በጀት የለም በሚሉ ሁኔታዎች ከዋና መሥሪያ ቤት በደብዳቤ የሚገለጽ በመሆኑ ቅጥር ለመፈጸም ተቸግረናል።

- የሰአት መቆጣጠሪያ (አቴንዳንስ) በየዳይሬክቶሬቱ ሥርና በየስራ ዘርፉ እንዲቀመጥ በኮሌጁ ሥራ አመራር በኩል ተወስኖ ስለሚሰራ ለቁጥጥርና ለክትትል አስቸጋሪ ሆኗል። ሆኖም ለወደፊቱ በማሻሻያ ሀሳቡ በተሰጠው አስተያየት መሰረት የምናስተካክል ይሆናል።

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት በኮሌጁ ኃላፊዎችና ሰራተኞች ስለተደረገልን መልካም የሥራ ትብብር እናመሰግናለን!!

**አባሪ. 1**

**መደበኛ የሒሳብ ሚዛናቸውን ያልጠበቁ ሂሳቦች ዝርዝር፤**

| ሂሳብ መደብ | የጥሬ ገንዘብ እና የተሰብሳቢ ሂሳብ | | |
|---|---|---|---|
| | ተቀጽላ ሌጀር | Opening balance ሐምሌ 1 ቀን 2008 ዓ.ም | Ending balance ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም |
| 1. ከካፒታል ሂሳብ | | | |
| 4101 | 01 | 292,300.12 | 292,300.12 |
| 4101 | 14 | 1,067.50 | 1,067.50 |
| የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ድምር | | 293,367.62 | 293,367.62 |
| 4211 | 003 | 118,758.47 | 118,758.47 |
| 4211 | 004 | 0.00 | 3,091.55 |
| 4211 | 008 | 185,319.89 | 182,228.34 |
| 4211 | 009 | 545,486.08 | 545,486.08 |
| 4211 | 44 | 0.00 | 13,750.00 |
| 4211 | 051 | 0.09 | 0.09 |
| 4211 | 174 | 214,781.46 | 214,781.46 |
| 4211 | 60 | 798,183.08 | 774,130.37 |
| 4211 | 200 | 0.00 | 166,278.78 |
| ድምር | | 1,862,529.07 | 2,018,505.14 |
| 2. ከውስጥ ገቢ ሂሳብ | | | |
| 4203 | 04 | | 270 |
| 4203 | 265 | | 2,052.00 |
| ድምር | | | 2,322.00 |
| 4211 | 008 | | 11,042.70 |
| 4211 | 44 | | 30,050.00 |
| 4211 | 174 | 265,929.35 | 265,929.35 |
| 4211 | 175 | 29,275.70 | 29,275.70 |
| 4211 | 200 | 897.00 | 897.00 |
| ድምር | | 296,102.05 | 337,194.75 |
| የተሰብሳቢ ሂሳብ ጠቅላላ ድምር | | 2,158,631.12 | 2,358,021.89 |

አባሪ. 2

<u>የተሰብሳቢ ሒሳብን የቆይታ ጊዜ የሚያሳይ ዝርዝር፤</u>

| ተራ ቁጥር | የሂሳብ መደብ ቁጥር | የተሰብሳቢ ሂሳቡ ክፍያ የቆይታ ጊዜ | የቆይታው ጊዜ | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ድረስ የቆየ | ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ድረስ የቆየ | |
| **I.** | ከካፒታል በጀት | | | | |
| 1 | 4203 | ከ2007 እስከ 2009 በጀት ድረስ | 179,137.50 | 318,662.87 | 497,800.37 |
| 2 | 4211 | ከ2008 እስከ 2009 በጀት ድረስ | 10,957.10 | | 10,957.10 |
| 3 | 4251 | ከ2007 እስከ 2009 በጀት ድረስ | | 75,523.59 | 75,523.59 |
| | | ድምር | 190,094.60 | 394,186.46 | 584,281.06 |
| **II.** | ከውስጥ ገቢ በጀት | | | | |
| 1 | 4203 | ከ2008 እስከ 2009 በጀት ድረስ | 140,768.57 | | 140,768.57 |
| 2 | 4210 | ከ2008 እስከ 2009 በጀት ድረስ | 80,000.00 | | 80,000.00 |
| 3 | 4211 | ከ2007 እስከ 2009 በጀት ድረስ | 274,308.71 | 64,184.00 | 338,492.71 |
| | | ድምር | 495,077.28 | 64,184.00 | 559,261.28 |
| | | ጠቅላላ ድምር | **685,171.88** | **458,370.46** | **1,143,542.34** |

አባሪ. 3

**<u>የተከፋይ ሒሳብን የቆይታ ጊዜ የሚያሳይ ዝርዝር፤</u>**

| ተራ ቁጥር | የሂሳብ መደብ ቁጥር | የተከፋይ ሂሳቡ የቆይታ ጊዜ | የቆይታው ጊዜ | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ድረስ የቆየ | ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ድረስ የቆየ | |
| **I.** | ከካፒታል በጀት | | | | |
| 1 | 5005 | ከ2008 እስከ 2009 በጀት ድረስ | 10,928.92 | | 10,928.92 |
| 2 | 5059 | ከ2008 እስከ 2009 በጀት ድረስ | 46,770.93 | | 46,770.93 |
| 3 | 5061 | ከ2008 እስከ 2009 በጀት ድረስ | 16,999.91 | 5,928.14 | 22,928.05 |
| | | ድምር | **74,699.76** | **5,928.14** | **80,627.90** |
| **II.** | ከውስጥ ገቢ በጀት | | | | |
| 1 | 5005 | ከ2008 እስከ 2009 በጀት ድረስ | 895.00 | | 895.00 |
| 2 | 5006 | ከ2008 እስከ 2009 በጀት ድረስ | 1,754.46 | | 1,754.46 |
| 3 | 5028 | ከ2008 እስከ 2009 በጀት ድረስ | | 4,959.55 | 4,959.55 |
| 4 | 5054 | ከ2008 እስከ 2009 በጀት ድረስ | | 340,000.00 | 340,000.00 |
| 5 | 5059 | ከ2008 እስከ 2009 በጀት ድረስ | 71,147.60 | 12,251.14 | 83,398.74 |
| 6 | 6061 | ከ2008 እስከ 2009 በጀት ድረስ | | 17,938.44 | 17,938.44 |
| | | ድምር | **73,797.06** | **375,149.13** | **448,946.19** |
